# Fund for Racial Equity የሳመር 2024 የስጦታ መቀበያ ዕድል
# በተደጋጋሚ የሚጠየቁ ጥያቄዎች

<u>የ Fund for Racial Equity ምንድነው ለምንስ ተቋቋመ?</u>
የማሕበራዊና ኢኮኖሚካዊ ዕድሎችንና ጤናንና ደህንነትን ለሁሉም ነዋሪዎች እንዳይዳረሱ የዘር ልዩነት ትልቁ እንቅፋት እንደሆነ በደምብ የተረጋገጠ ሓቅ ነው። በዘር ምክንያት የሚፈጸምን ግፍ በመታገል፣ ለሁሉም የአሌክሳንድሪያ ነዋሪ የተሻለ ከተማ እንፈጥራለን። የ Fund for Racial Equity፣ ይህንን በግምት ውስጥ በማስገባትና ስርዓታዊ ዘረኝነትን ለማፍረስና በአሌክሳንድሪያ ከተማ ውስጥ የዘር እኩልነትን ለማስፈን ተብለው የሚደረጉ ጥረቶችን ለመደገፍ ተብሎ ነው። የ Fund for Racial Equity ስጦታዎችን የሚሰጥበት መንገድ የ Community Advisory Board ምሪትን ተከትሎ ነው።

<u>የዘር እኩል አለመሆን ሲባል ምን ማለት ነው?</u>
የዘር እኩል አለመሆን የሚኖረው፣ የአንድ ሰው የዘሩ መለያ በህይወቱ ውስጥ ሊኖሩት የሚችሉትን ውጤቶችን ሊተነብይ የሚችል ሲሆን ነው። የዘር እኩል አለመሆን፣ በተለያዩ የዘር ቡድኖች ውስጥ የተለያዩ ውጤቶችን ሊያስከትሉ በሚችሉ ማሕበራዊ፣ ባህላዊ፣ ፖለቲካዊና ታሪክዊ ሁኔታዎች ላይ ይንጸባረቃሉ። የዘር እኩል አለመሆን፣ በትምህርት (የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የምረቃ ደረጃ) ፣ ስራ (የስራ ዓጥነት ደረጃ)፣ የወንጀለኛ ፍትህ (የእስር ደረጃ)፣ የህይወት ዘመንና፣ በሌሎች የስኬታማነት ማመልከቻ፣ በታላቅ ደረጃ በግልጽ ይታያሉ። ከ ዘርና ማሕበራዊ እኩልነት ጋር በተዛመደ መግለጫዎችን* ከፈለጉ ሊንኩን ይጠቀሙ።

<u>ስርዓታዊ ዘረኝነት ሲባል ምን ማለት ነው?</u>
ይህ በግለሰቡ፣ በተቋሞችና መዋቅራዊ ደረጃ መሃል ያለ እርስ በእርሱ የተገናኘና ተመላላሽ የሆነ ግንኙነት ያለው፣ የዘረኝነት ሲስተም ሆኖ የሚያገለግል ዝምድና ነው። እነዚህ የተለያዩ ደረጃዎች ያሉት ዘረኝነት፣ እንደ አንድ የተደራጀ ሞዴል በአንድ ላይ እንደ አንድ የተሟላ ሲስተም የሚሰራ ነው። እነዚም ደረጃዎች የሚከተሉት ናቸው፤

- ግለሰቡ (በሰዎች መሃል ያሉ ግንኙነቶች)
- ተቋማዊ (በተቋሞችና ስልጣን ባላቸው ሲስተሞች መሃል ውስጥ)
- መዋቅራዊ ወይም ማህበራዊ  (በተቋሞችና በማሕበረሰብ ውስጥ)

* https://www.alexandriava.gov/equity/race-and-social-equity-definitions

**ይህ የስጦታ ዕድል**

<u>የነዚህ ስጦታዎች ዓላማ ምንድነው?</u>
የነዚህ ስጦታዎች ዓላማ በአሌክሳንድሪያ ከተማ ውስጥ የዘር እኩልነትን አመልክቶ የሚደረጉ ጥረቶችን ለመደገፍ ሲሆን። በተለይም የልጅ ደህንነት፣ ትምህርትት፣ ጤናና የመኖሪያ ቤት ሁኔታዎችን በማሻሻል ላይ ልዩ ትኩረት ያደርጋል።

<u>ስጦታው የሚያተኩርባቸው የትኞቹ ላይ ነው?</u>
ይህ Community Advisory Board፣ ቅድሚያነት የሚሰጠው ስጦታው በሚያተኩርባቸው አካባቢዎች ላይ፣ ስጦታው ጋር የተያያዙ ተግባሮችን በመፈጸም ወቅት እኩልነትን ማእከል አድርገው የሚደረጉ ጥረቶችንና፣ በመዋቅራዊ ዘረኝነት እጅግ ለተጎዱት ኤጀንሲ ለሚገነቡ ጥረቶች ይሆናል።

<u>ስጦታው ድጋፍ ሊሰጥ የሚችለው ለምን ዓይነት ፕሮግራሞች ነው?</u>
እነዚህ ስጦታዎች የሚሰጡት በየ  ACT፣ የ Fund for Racial Equity ሆኖ፣ ትኩረታቸው በመኖሪያ ቤትሥ ትምህርት፣ ጤናና የልጅ ደህንነት ኣካባቢዎች ላይ እኩልነት ወደሚያደርስ እድገት ትኩረት አድርገው ለሚሰሩ ይሆናል። በነዚህ አካባቢዎች ውስጥ ለውጥን ለማምጣት የሚሰሩ ፕሮግራሞች ለዚህ ስጦታ ግምት ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ።

<u>ለዚህ ስጦታ ማን ማመልከት ይችላል?</u>
ግለሰብ ነዋሪዎችና ያለ-ትርፍ የሚሰሩ ድርጅቶች ለዚህ ስጦታ ለማመልከት ብቁ ናቸው። ግለሰቦች ያላቸው የዘር መለያ ምን እንደሆነ በግምት ሳይገባ ማመልከት ይችላሉ፣ እንዲሁም በአለክሳንድሪያ የግድ መኖር የለባቸውም። እድሜያቸው 16 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማመልከት ይችላሉ። ቢሆንም፣ ዕድሜያቸው ከ 18 በታች የሆኑት የወላጅ/ አሳዳጊ ፈቃድ ያስፈልጋቸዋል።

<u>ስጦታውን ለመስጠት ውሳኔዎች መቼ ነው የሚፈጸሙት?</u>
ስጦታዎችን ለመስጠት ውሳኔ በሴፕቴምበር 2024 መጨረሻ ላይ ይደረጋል ተብሎ ይጠበቃል።

<u>ከፍተኛው የስጦታ መጠንና የስጦታው የግዜ መጠን ምን ያህል ነው?</u>
ከፍተኛው የስጦታ መጠን $2,000 ነው። የስጦታው ግዜም፣ ስጦታውን ከተቀበሉበት ቀን ጀምሮ ለአንድ ዓመት ነው።

<u>ስጦታው እንደ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተደርጎ ይቆጠራል ወይ?</u>
አዎ፣ በስጦታ የሚሰጥ ገንዘብ እንደ ግብር የሚከፈልበት ገቢ ተደርጎ ነው የሚቆጠረው። የስጦታ መጠኑ የሚወሰነው ለማሕበረሰባዊ ድርጅቶች ወጪ መሸፈና ብሎ በፈቀደው የ ACT for Alexandria መመሪያ ይሆናል።

*<u>ገንዘቡን እንዴት እንዳጠፋሁት ለማሳየት ደረሰኞችን ማሳየት ያስፈልገኛል ወይ?</u>*
አይ፣ ደረሰኞችን ማሳየት አያስፈልግም። የ ACT for Alexandria ሰራተኞችና የ Fund for Racial Equity Community Advisory Board አባሎ፣ ጥረትዎን (ስኬታማነትንና ሌሎችን) በየትኛው መንገድ ይበልጥ መገምገም እንደሚቻል ለመወሰን አብሮዎት ይሰራሉ።

Updated July 24 2024

**ለስጦታው ማመልከቻ ማስገባት**

<u>እንዴት ማመልከቻ የማስገባው?</u>

እርስዎ በሚፈልጉት ቋንቋ የተዘጋጀ ማመልከቻ ለማግኘት፣ የ ACT for Alexandria Fund for Racial Equity ድረገጽ** ን ይጎብኙ። የወረቀት ማመልከቻም ወደ ACT for Alexandria ቢሮ (በ ALX Community Waterfront Building, 201 N. Union St. Suite 110, Alexandria, Virginia 22314 ውስጥ)፣ በመደበኛ የስራ ሰዓታት ላይ (9am-5pm ሰኞ- ዓርብ) በመሄድ መውሰድ ይችላሉ። ማመልከቻውን እርስዎ በሚፈልጉት ቋንቋ ታይፕ ሊያደርጉት ወይም በእጅ ሊሞሉት ይችላሉ። እንዲሁም ደግሞ በኤሌክትሮኒክ መንገድ ወይም ፕሪንት ተደርጎ በሚከተለው መልክ ሊገባ ይችላል፤

- በኤሌክትሮኒክ፤ ማመልከቻውን ከድረገጹ ዳውንሎድና ሴይቭ ያድርጉ። አንዴ ሞልተውና ፊርማዎን ማመልከቻው ላይ ካጸደቁ በኋላ፣ ወደ grants@actforalexandria.org ኢሜይል ያድርጉት። ስራዎን በተደጋጋሚ ሴይቭ ማድረጉን አይርሱ።
- የወረቀት ማመልከቻ፤ የወረቀት ማመልከቻ ወደ ACT for Alexandria offices (201 N. Union St., Suite 110, Alexandria, Virginia 22314) በፖስታ ሊላኩ ወይም በመደበኛ የስራ ሰዓታት ላይ (9am-5pm፣ ሰኞ-ዓርብ) ሊሰጡ ይችላሉ።

በተጨማሪም፣ በአካል የሚሰጥ የማመልከቻ ድጋፍ በ ACT for Alexandria ቢሮዎች (201 N. Union St., Suite 110, Alexandria, Virginia 22314) ከ 3:00-5:00pm ጁላይ 29 እስከ ኦገስት 2፣ ኦገስት 13-16፣ እና ኦገስት 20-21 ድረስ ይኖራል። የቋንቋ አገልግሎት እርዳታ ይኖራል።

***ማመልከቻ እስከ 5:00pm ኦገስት 22, 2024 ባለው ግዜ ውስጥ መድረስ ይኖርበታል።***

<u>ማመልከቻ በመሙላት ላይ ጥያቄ ካለኝ ወይም እርዳታ ካስፈለገኝ ማንን ማናገር እችላለሁኝ?</u>

ማመልከቻውን አስመልክቶ ጥያቄዎች ካልዎ፣ ይህንን ሰነድ መመልከት ይችላሉ፣ በ Fund for Racial Equity ድረገጽ ላይ የተዘጋጀውን የመረጃ መስጫ ቪድዮ መመልከት ወይም ከ ACT for Alexandria ጋራ በ grants@actforalexandria.org ወይም 703-739-7778 መገናኘት ይችላሉ። በ Fund for Racial Equity ድረገጽ ላይ የቢሮ ሰዓታት ይለጠፋል እንዲሁም የቋንቋ አገልግሎት እርዳታም ይኖራል።

<u>ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ማመልከቻ ማስገባት እችላለሁኝ ወይ?</u>

አይ፣ ለአንድ ሰው ወይም ያለ-ትርፍ የሚሰራ ድርጅት አንድ ማመልከቻ ብቻ ነው የምንቀበለው።

<u>በአንድ ድርጅት ውስጥ ያሉ የተለያዩ ሰዎች ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ ወይ?</u>

አዎ፣ በአንድ ድርጅት ውስጥ የተለያዩ ሰዎች በግለሰብ ደረጃ ማመልከቻ ማስገባት ይችላሉ። ቢሆንም ለተለያዩ ፕሮጀክቶች ማመልከቻ ማስገባት ይኖርባቸዋል።

** https://www.actforalexandria.org/initiatives/t/fund-for-racial-equity/